# ጥናት አንድ ዕንባቆም 1:1-17 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እንባቆም እግዚአብሄርን የሚጠይቃቸው ጥያቄዎች፡ ለእርዳታ እየተጣራሁ የማትሰማው እስከመቼ ነው? የማታድነውስ እስከመቼ ነው? ለምን በደልን እንዳይ አደረግሽኝ? እንዴት ግፍ ሲፈጸም ትታገሳለህ? የሚሉት ናቸው። ይህ አባባሉ የሚጠቁመን ይህ ነገር የአጭር ጊዜ ሳይሆን ለረጅም ጊዜ የተመለከተው ነገር እንደሆነ መረዳት ይቻላል።
2. እንባቆም እያየ ያለው ነገር፡ ጥፋትና ግፍ ሲፈጸም ያያል፣ ጠብና ግጭት እየበዛ ሲሄድ፣ ሕግ ሲላላ፣ ፍትህ ድል ሲነሳ፣ ፍትህ ሲጣመምና፣ ክፉዎች ጻድቃንን ሲከቡ ዘወትር ይመለከታል። እንባቆም ተገቢውን እርምጃ ወስዷል ብዬ አምናለሁ፤ ምክንያቱ እንደ ሰው ማድረግ የሚችለው ነገር ሁሉን ማድረግ ወደሚችለው ወደ እግዚአብሄር እንደጸለየ በቁ2 ላይ እናነባለን።
3. እንባቆም ችግሩን ለመፍታት የወሰደው እርምጃ ምንም ፍሬ እንዳላፈራ ነው የማየው፤ ምክንያቱም የጸለየው ጸሎት ወይም ከእግዚአብሄር የእርዳታ ጥያቄው እንዳልተሰማ፣ የእግዚአብሄርን ማዳን እንዳላየ፣ ግፍ ሲፈጸምም ሁሉ እግዚአብሄርም ራሱ በግድ የለሽነት እየተመለከተ እንደሆነ ነው እንባቆም የገባው። እንባቆምን የሚያንገበግበውና ዋጋ የሚሰጠው ከጥያቄዎቹ የምንረዳው አንድ ነገር የእግዚአብሄር ቅድስና የሚለው ሃሳብ ይመስለኛል፤ ይኸውም እግዚአብሄር ቅዱስ አምላክ ሆኖ ሳለ ገፍንና በደልን መታገሱ ለእንባቆም እንቆቅልሽ ሆኖበታል።
4. እግዚአብሄር በቁ5-11 ላይ ለእንባቆም የነገረው ነገር በነብዩ የተጠየቀውን ለምን ይህንን ሁሉ ግፍና ጭካኔ ፍትህ መጓደል እየተመለከትክ ዝም ትላለህ ለሚለው ባቢሎናውያን መጥተው ግፈኞቹንና ክፉ አድራጊዎቹን ሁሉ እንደሚቀጡ በመናገር መልስ ሆኖታል። ለእንባቆም በአንድ በኩል ጥያቄውን ቢመልስለትም በሌላ በኩል ግን ከፊተኛው የበለጠ ጥያቄ እንደፈጠረበት ከቁ12 ጀምሮ ከሚናገራቸው አነጋገሮች ማየት እንችላለን።
5. ጨካኞች ቁ6፣ የሚያስፈሩና የሚያስደነግጡ ቁ7፣ ፍርዳቸውና ክብራቸው ከራሳቸው የሚወጣ ህዝብ ናቸው ቁ7፣ ነጣቂ አሞራ ቁ8፣ ለአመጽ የታጠቁ ቁ9፣ የሚንቁና፣ የሚያፌዙና የሚስቁ ቁ10፣ ጉልበታቸውን አምላካቸው ያደረጉ በደለኞች ናቸው ቁ11። በነብዩ ዓይን ስንመለከተው ትክክለኛ መልስ ሊሆኑ የማይችሉት ሃጥያተኞችን ለመቅጣት ሌላ ሃጥያተኛን መጠቀም እግዚአብሄራዊ አሰራር ስለማይመስል ነው።
6. እግዚአብሄር ከዘለዓለም ጀምሮ ያለ አምላክ፣ ቅዱስ እንደሆነ፣ መሾም የሚችል መሆኑን፣ ሥልጣን መስጠት እንደሚችል፣ ንጹህ ዓይን ያለው፣ በደልን መታገስ የማይችል አድርጎ ያየዋል። ሌሎቹ የእንባቆም ጥያቄዎች በቁ13 ላይ የምናነባቸው፡ ‹‹…አታላዮችን ለምን ትታገሳለህ?››፣ ‹‹ክፉው ከራሱ ይልቅ ጻድቅ የሆነውን ሲውጠውስ ለምን ዝም ትላለህ?›› የሚሉት ናቸው።
7. እግዚአብሄር በሰዎች መሃል ስለሚካሄደው ነገር ምንም ግድ የማይሰጠው፣ የሚካሄደውን ነገር ሁሉ ዝም ብሎ የሚመለከት እንደሆነ የሚያስብ ይመስላል ከአነጋገሩ። እንባቆም ከእግዚአብሄር የሰማው መልስ በጭራሽ የጠበቀው ዓይነት መልስ አይመስለኝም፣ ምክንያቱም በቁ13 ላይ መልሱ በነብዩ አዕምሮ ውስጥ ሌላ ከበፊቱ የበለጠ ጥያቄን ሲያስከትል ስለማይ ነው።
8. ነብዩ እንባቆም ለምን ጥያቄ በአዕምሮህ መጣ ወይም ለምን ጠየከኝ በሚል እግዚአብሄር አንድም ጊዜ እንዳልተቆጣውና ለጥያቄው መልስ እንደሰጠው እንመለከታለን።

# ጥናት ሁለት ዕንባቆም 2፡1-20 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ነብዩ ሊያደርግ የወሰነው ነገር፤ በመጠበቂያው ላይ በመቆም፣ በምሽጉ ቅጥር ላይ በመውጣት እግዚአብሄር ምን እንደሚለው ለመስማትና ለማወቅ ለመጠባበቅ ነው የወሰነው። ኢሳይያስ ሲናገር የጊዜውን ቅርበትና ርቀት ሳያነሳ አንድ ቀን የሚሆን ነገር እንደሆነ አድርጎ ነው የተናገረው፤ በዚህ ክፍል ግን ነገሩ እንደማይዘገይና በቅርቡ በእርግጠኛነት የሚፈጸም ነገር እንደሆነ ነው የተነገረው።
2. በቁ2 ላይ በቀላሉ እንዲነበብ መፈለጉ፣ ራዕዩ እንዲጻፍ መፈለጉና፣ በሰሌዳም ላይ እንዲሰፍር መፈለጉ ይህንን ያረጋግጣል። እግዚአብሔር የሰጠው መልዕክት የማያሻማና ለመረዳት እንደማያስቸግር የሚያሳየን ቃል በቁ2 ላይ የምናነበው ‹‹በቀላሉ እንዲነበብ ራዕዩን ጻፈው›› የሚለው አነጋገር ነው።
3. በተለያዩ ነብያት የተነገረው በባቢሎን የመገዛት ትንቢት እስከዛሬ ለቆየበት ምክንያት ለነብዩ መልስ ይሆናል። እግዚአብሄር በምዕ1 ውስጥ የሰጠው መፍትሔ ለብዙ ዘመናት በተለያዩ ነብያት የተነገረ ሲሆን፤ እስከዛሬ ያልተፈጸመና ሆኖ ያስታየ ቢሆንም እንኳን፤ እግዚአብሄር ጊዜው ያለፈና የማይሆን መስሎ በሚታይበትም ጊዜ ጭምር በእምነት በእርሱ ቃል ላይ መቆም አማራጭ የሌለው ነገር እንደሆነ ለራሱ ሲያረጋግጥ ነው።
4. ይህ ወዮታ የተጻፈው ቁ6 እንደሚነግረን ‹‹የተሰረቀውን ሸቀጥ ለራሱ ለሚያከማች፣ ራሱን በዓመጽ ባለጠጋ ለሚያደርግ›› ብሎ ይነግረናል። ሁለተኛው ወዮታ የሚገኘው በቁ9 ላይ ሲሆን ያተኮረውም በተጭበረበረ ትርፍ መኖሪያውን ለሚሰራና ከጠላት ለማምለጥ ቤቱን በከፍታ ላይ ለሚሰራ ነው ይለናል።
5. በቁ12 ላይ ያለው ወዮታ ከተማን ደም በማፍሰስ ለሚሰሩና በወንጀል ከተማን ለሚመሰርቱ የተጻፈ ነው። እግዚአብሄር የወሰነው ብሎ ነብዩ የሚነግረን በቁ13 ላይ የምናየው የባቢሎን ሰዎች ከተማን በመመስረት ልፋታቸውና የህዝብ ሁሉ ድካም ለእሳት ማገዶነት እንደሆነ እግዚአብሄር ሲናገር፤ በሌላ በኩል ደግሞ ውሃ ምድርን እንደሚሸፍን ምድር የእግዚአብሄርን ክብር በማወቅ የምትሞላበት ጊዜ እንደሚመጣ ይነግረናል።
6. እነዚህ ሰዎች የባልንጀሮቻቸውን ሃፍረተ ሥጋ ለማየት ያደረጉአቸው ድርጊቶች ሁሉ ሌሎች ደግሞ በእነርሱ ላይ ማድረጋቸው፤ ሰው የዘራውን ያንኑ እንደሚያጭድ በገላትያ ላይ የተነገረው እውነት ማረጋገጫ ሆኖ አየዋለሁ።
7. ይህ የመጨረሻ ዋይታ የተነገረው፤ ጣዖት አድርገው የሰሩትን እንጨት ንቃ ለሚሉ፣ ሕይወት የሌለውንም ድንጋይ ተነሳ ለሚሉት ሰዎች ነው። በዚህ ቁጥር ላይ ነብዩ ሰዎቹን የሚጠይቃቸው ጥያቄ ‹‹በውኑ ማስተማር ይቻላልን?›› የሚል ነው። ይህንን ሲል እነርሱ የሰሩት ጣዖት አስተምረውና አለማምደው አምላክ ለማድረግ ልታበቁት ትችላላችሁ ወይ? ማለቱ ይመስለኛል። ለራሱ የመለሰው መልስ፤ በወርቅና በብር ተለብጧል እንጂ እስትንፋስ እንደሌለውና ሊያስተምሩት እንደማይችሉ ነው።
8. በቁ20 ላይ ‹‹እግዚአብሄር ግን..›› የሚለው ከላይ ሰው ለራሱ አምላክ አድርጎ ከሚያቆማቸው ህይወት ከሌላቸውና ምውት ከሆኑት ጣዖታት ጋራ በማነጻጸር ነው። ከዚህ እንባቆም ለራሱ የሚያስተላልፈው መልዕክት ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ የሆኑ በሚመስለኝ ጊዜ ጭምር እርሱ በተቀደሰ መቅደሱ ሆኖ ፍጥረትን ስለሚያስተዳድር በጸጥታና በመታመን መቆየት እንደሚኖርበት እንደተማረ ነው የማየው።

# ጥናት ሶስት ዕንባቆም 3:1-19 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እንባቆም በቁ2 ላይ የእግዚአብሄርን ዝና እንደሰማና እግዚአብሄር የሰራውን ስራ ሲያስብ እግዚአብሄርን እንዲፈራ እንዳደረገው እናነባለን። ነብዩ እግዚአብሄርን የሚጠይቃቸው ነገሮች በእነርሱም ዘመን ጥንት የሰራቸውን ስራዎች እንዲሰራ፣ እነዚህ ሥራዎቹም በእነርሱ ዘንድ ለህዝቡ እንዲታወቁ እንዲያደርግና፤ ሌላው ደግሞ መዓት ሊመጣባቸው እንደሆነ ቢያውቅም በዚህ ውስጥም ምህረቱን እንዲያስብ ይለምነዋል።
2. በቁ13 ላይ ህዝቡን ለመታደግ እንደወጣ፣ የክፋትን ምድር መሪ እንደቀጠቀጠና ከራስ ጠጉሩ እስከ እግር ጥፍሩም ድረስ እርቃኑን እንዳስቀረው የሚናገረው አነጋገር፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ ከሙታን በመነሳቱ ምክንያት በጠላታችን ላይ የደረሰውን ሽንፈት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየንን ነገር ነው የተናገረው።
3. መጥቶባቸው የነበረውን የጠላት ዓይነት ሲገልጽ እንባቆም፤ እንደ አውሎ ነፋስ ሊበታትናቸው የመጣ እንደነበረ፣ ምስኪኑን በስውር በመዋጥ ደስታ የሚያገኝ ዓይነት ጠላትም እንደነበረም ይነግረናል። እግዚአብሄር አምላክ ይህንን ክፉና ጨካኝ የሆነውን ጠላታቸውን ከመንገድ ለማስወገድ የተጠቀመበት መንገድ፤ ዋነኛውን የሰራዊቱን አለቃ ራስ በገዛ ራሱ ጦር ተጠቅሞ በመውጋት እንደነበረ ነው ነብዩ የሚነግረን።
4. እንባቆም በዚህ ቁጥር ላይ ሰማሁ በማለት የሚናገረው ነገር ለእኔ እንደገባኝና ከአነጋገሩ እንደምረዳው ከሆነ በዚሁ ቁጥር ውስጥ ወራሪ እንደሚመጣባቸው እግዚአብሄር አስቀድሞ በምዕራፍ አንድ ውስጥ ስለባቢሎን ሰራዊት የነገረውን ሃሳብ ይመስለኛል። እንባቆም ከሰማው ነገር የተነሳ ልቡ እንደደነገጠበት፣ ከንፈሩ እንደተንቀጠቀጠበት፣ ፍርሃት እስከ አጥንቱ ድረስ ዘልቆ እንደገባና እግሩም እንደተብረከረከበት እናነባለን።
5. በቁ17 ላይ የተዘረዘሩት ነገሮች፤ የበለስ አለማፍራት፣ የወይን ተክል ፍሬ አለመስጠት፣ በወይራ ዛፍ ፍሬ አለመገኘት፣ የእርሻ ሰብል አለመስጠት፣ በጎች በጉረኖ አለመኖርና ላሞች በበረት ውስጥ አለመኖር የሚሉት ናቸው። በጥናቱ ላይ ከሚገኙት ተሳታፊዎች ሁሉ የሚመጡትን በማስተናገድ ሰፋ ያለ ውይይት አካሂዱ።
6. እንደነዚህ ዓይነት ነገሮች በሰዎች ህይወት ውስጥ ሲከሰቱ የሚያስከትሉት ስሜት ከልብ ውስጥ ደስታን ሰርቆ በሃዘን መሙላት እንደሆነ ከኢዩኤል ምንባብ እንረዳለን። ዕንባቆም የነዚህ ነገሮች ሁሉ መሆን ስሜቱን በሃዘን እንዳይሞሉት የተጠቀመበት መንገድ ትኩረቱን በነዚህ በጠፉ ነገሮች ላይ ከማድረግ ይልቅ በእግዚአብሄር ላይ ለማድረግ መወሰኑ እንደሆነ በዚህ ቁጥር ላይ እናነባለን።
7. በዚህ ቁጥር ላይ ‹‹እኔ ግን›› ሲል በተለይ በኢዩኤል 1:12 የምናያቸው ሰዎች ደስታቸውንና የልባቸውን ዝማሬ የሚያጠፋው ነገር የሚበላ፣ የሚጠጣና የሚለበሰው ነገር ከሆነላቸው ጋራ ራሱን ሲያነጻጽር እንደሆነ ይመስለኛል። እግዚአብሄር ለዚህ ሰው ሃይሉ ነው፣ እግሮቹንም እደዋላ እግሮች በማድረግ በከፍታዎች ላይ እንደሚያስኬደውም ይነግረናል።
8. እንባቆም ደስታውና ሃሴት የሚያደርገው በእግዚአብሄር እንደሆነ ግልጽ አድርጎ ነው የሚናገረው።

By Wondimu Habtewold (253) 653-4707 